# የአንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ ከምድረክ ጋር ሲኖረው የሚገባውን ግንኙነት አስመልክቶ በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረው ውዝግብ

ሽመልስ ተክለ-ጻድቅ ዶ/ር
የአንድነት ብሔራዊ ም/ቤት ሰብሳቢ

## 1. መግቢያ

- የዚህ ጽሑፍ ዋና አላማ የአንድነትን ፓርቲ መተዳደሪይ ደንብና ስነ ስርዓት ማስከበርና በዚህም ጥረት የፓርቲያችንን ድርጅታዊና ፖለቲካዊ አቋም ሙሉነትና ነፃነት ማረጋገጥ ነው።
- የአንድነት ፓርቲ በፖለቲካ ፕሮግራሙ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.3 ላይ እንደሰፈረው «ሀገራዊ የትግል አንድነትን ለማጠናከር በዴሞክራሲያዊ መንገድ ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር የተለያዩ የትግል ግንኙነቶችን ሊፈጥር ይችላል፣ ማንኛውም የፖለቲካ ልዩነት በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈታ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።» በመርህ ደረጃ እንዲህ ያስቀመጠውን አፈጻጸሙን በሚመለከት ደሞ:-
  1. የአንድነት ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 11.10 የሚለው ም/ቤቱ «ፓርቲው ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚመሠርታቸውን ከህብረት እስከ ውህደት የሚደርሱ የትግል ግንኙነቶችን በተመለከተ ስምምነት ይፈጽማል። ይህንኑም ለጠቅላላ ጉባዔው ያሳውቃል» ነው።
  2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ግዴታም በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 14.10 እንደዚህ ተቀምጧል። «ከመሰልና አቻ ድርጅቶች ጋር ሲኖር የሚጋባን የትግል ግንኙነት በተመለከተ የብሔራዊ ም/ቤቱን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል።»

## 2. ከመድረክ ጋር አንድነት ፓርቲ ስለሚኖረው የወደፊት ግንኙነት በብሔራዊ ምክር ቤቱ የተካሄዱ ስብሰባዎች:-

- የየካቲት 9 ም/ቤት ስብሰባ ቃለ ጉባዔ የሚያመለክተው
  1. የፓርቲው ዋና ጸሐፊ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ወክለው በስብሰባው መጀመሪያ ላይ የማቀርበው መረጃ አለኝ ብለው የመናገር እድሉ ሲሰጣቸው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከመድረክ ጋር ለመቀላቀል ወስኗል ብለው ተናገሩ፣
  2. ውይይቱ ጠንከር ባለ ሁኔታ ሲካሄድ ጥያቄዎችና ተቃውሞች ሲበዙ ደግሞ ከሌሎቹ የስራ ባለደረቦቻቸው ጋር በመተጋገዝ የለም አልወሰንንም ጥያቄውን ለም/ቤቱ ያቀረብነው ለውሳኔ ነው አሉ፣
  3. ም/ቤቱም፣ እንግዲያው፣ ለውሳኔ የሚረዱ ሰነዶች ሁሉ ተዘጋጅተው ለአባለት እንዲታደሉ ጽ/ቤቱን አዞ ለውሳኔ ሌላ የስብሰባ ቀን ተያዘ።
- የየካቲት 30 ም/ቤት ስብሰባ ቃለ ጉባዔ የሚያመለክተው
  1. በዚህም ስብሰባ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን በመወከል በዋና ጸሐፊው የቀረበው መረጃ:- 1. መድረክ የሚባል ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት የለም፣ 2. ለዛሬው ም/ቤት ስብሰባ ውሳኔ ይረዳ ዘንድ ያደልናችሁም የለም፣ 2. ለዛሬው ም/ቤት ስብሰባ ውሳኔ ይረዳ ዘንድ ያደልናችሁም የለም፣ «መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ (የምክክር መድረክ) «መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ» የሚባልና የሚሰራ ሰነድ የለም፣ 3. ስለሆነም የውስጥ አሰራር ደንብ» የሚባልና የሚሰራ ሰነድ የለም፣ 3. ስለሆነም የውስጥ አሰራር መዋቅራዊም ሆነ ደንባዊ ወሰን ከእንግዲህ ያለምንም ገደብና የአሰራር መዋቅራዊም ሆነ ደንባዊ ወሰን ከመድረክ ጋራ አብሮ መስራት ይቻላል የሚል ነበር።

2. አንዳንድ አባላት መድረክማ አለ ይታያል፣ መግለጫ ይሰጣል፣ ጥናታዊ የፖለቲካ ስብሰባ ያካሂዳል፣ ሌላ ሌላም ብዙ ተግባሮች ያካሂዳል ብለው ነበር።
3. ም/ቤቱም ሰፋና ሞቅ ያለ ውይይት ካካሄደ በኋላ የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ በድምጽ ብልጫ አሳለፈ፡-
<u>«መድረክን በተመለከተ የብሔራዊ ም/ቤቱ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከመድረክ ጋር በጋራ መስራት አስፈላጊ መሆኑን የገለጸውን በማመን የስራ አስፈጻሚውን ሃሳብ ተቀብሎታል። አፈጻጸሙን በተመለከተ የስራ አስፈጻሚው (አንዳስፈላጊነቱ የቴክኒካል ኮሚቴዎችን በመጨመር) የአንድነትን ፖለቲካዊ አላማ መሠረት አድርጎ ግንኙነት እንዲጀምር የተደረሰበትንም ስምምነት ለብ/ም ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ»።</u>

## <u>3. የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ. ም. በ«መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ» የተሰጠው መግለጫ</u>

- የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ. ም. «መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ» መግለጫ ሰጠ። በዚህም መግለጫ የአንድነት ፓርቲ የመድረክን «መርሆዎችና መመዘኛዎች» ስላሟላ መድረክን እንደተቀላቀለ አሳወቀ። እንዲሁም በተጨማሪ፣ የመድረኩን የወቅቱ ሊቀመንበርና ዋና ጸሐፊ መምረጡን፣ በመቀጠልም 4ኛ ጉባዔው ከየአባል ፓርቲዎቹ (አኛንም ጨምሮ ማለት ነው) አንድ አንድ አባላት በውክልና ሁለት ግለሰቦች ደሞ በራሳቸው የተወከሉበት ለመድረክ «ማኒፌስቶ» የሚያዘጋጅ አንድ ግብረ ኃይል ማቋቋሙን አበሰረን።
- እዚህ ቡድን ውስጥ በዴሞክራሲያዊ አሰራር ድምጽ አሰጣጥ ቀመር አንድነት 1/10ኛ ድምጽ ይኖረዋል ማለት ነው።
- እነዚህ አላይ የተጠቀሱት ውሳኔዎች በሙሉ በጉባዔው የተወሰዱት አሁን በቅጅ መልክ ባለው የድርጅቱ «የውስጥ አሰራር ደንብ» መሠረት ነው። በተለይ የሚገርመው ለመድረክ ጉባዔ ተቋምነትም ሆነ ለድርጅቱ ህልውና የሚሰጠው ዋናው የመድረኩ «መግባቢያ ሰነድ» (memorandum of understanding) መኖሩን የኛ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አያውቁም፣ ካወቁ ለም/ቤቱ አባለት እንዲደርስ አልፈለጉም።
- በዚህ የመድረክ መግለጫ አሰጣጥ ስነ ስርዓት ላይ የአንድነትን ብሔራዊ ስራ አስፈጻሚ–ኮሚቴ ከሚወክሉት ሶስት ሰዎች ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያምና አቶ አስራት ጣሴ በአካል ተገኝተው ነበር። የአንድነት ፓርቲን ሕጋዊ ማኅተምም የመግለጫው ጽሑፍ ላይ አስፍረዋል።
- በዚህም አድራጎታቸው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በወልና ኮሚቴውን ወክለው ከመድረክ ጋር ከወዲሁ ተቀላቅለው ስራ የጀመሩት ግለሰቦች የአንድነትን ፓርቲ ደንብና ስነ ስርዓት በመጣስ ነው።

## <u>4. ለአንድነት ፓርቲ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የወቅቱ ሊቀመንበር የጻፍኩት ደብዳቤ</u>

- ደብዳቤውን በአሁኑ ወቅት ሁላችሁም እንብባችሁታል የሚል ግምት አለኝ። ደብዳቤው በጋዜጣ ለመውጣትም በቅቷል። ሁላችሁም እንድታውቁልኝ የምጠይቀው ይህ ደብዳቤ ጋዜጣ ላይ በመውጣት ሂደት (ፎቶግራፍ መስጠትን ጨምሮ) በምንም መልኩ የኔ ፈቃድና ተሳትፎ እንደሌለበት ነው።
- ደብዳቤውን ጠንከር አድርጌ የጻፍኩት የመድረክ መግለጫ ውስጥ አላይ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሱት ውሳኔዎች በፓርቲያችን አባላትና በደጋፊዎቻችን መሃል ሊያደርስ የሚችለውን ብዥታና ቀውስ በመገመት አስቤና ሆን ብዬ ነው።

ደብዳቤውን ለሲቀመንበሩ ያደረሱት መድረክ እሳይ የተጠቀሰውን መግለጫ ከመስጠቱ 24 ሰዓት በፊት ነው።

- በዚያን ጊዜ በተጨማሪ ለሲቀመንበሩ በቃል የነገርኳቸው የመፍትሄ ሃሳብ እንዴት ቀላል እንደሆነ፣ እሱም፦ አንደኛ አንድነትን በተመለከተ ያረፈው አንድ መስመር የማይሞላና የመድረክ መግለጫን መሠረተ ሃሳብና ይዘት የማይቀይር ሃረግ ከመግለጫው ጽሑፍ ማውጣት፣ ሁለተኛ ድንገት የመድረክ መሪዎች የአንድነት መጠቀስ በጣም ያስፈልገናል ካሉ ከእውነቱ የማይርቅ ሃሳብ ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲም ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በመደራደር ላይ ነን ማለት እንደሚቻል በአጽንኦት ገለጽኩላቸው።
- ለሳቸው የሰጠሁትን ምክርና የመፍትሄ ሃሳብ ላገኘሁት የፓርቲያችን ከፍተኛ አመራር አካልና የብ/ም ቤት አባል በአጽንኦት ግፊት ለማድረግ ቀኑን ሙሉ ስጥር ነበር።

## 5. በፓርቲያችን መሃል የተፈጠረውን ውዝግብ ለማረም የሚያስችሉ እርምጃዎች፦

- ይህንን ችግር ሊፈታው የሚችለው ምክር ቤታችን ነው፣ ፓርቲያችን ከጅምሩ ም/ቤቱን ለመጠናከር የወሰደው እርምጃ የዚህን ዓይነት ችግሮች ለመፍታት እንዲችል ተገንዝቦና መክሮበት ነው።
- ም/ቤቱ አንድ የራሱ የሆነና የሰከነ ግንዛቤ ላይ ደርሶ፣ በተቻለ መጠን እንዲያው በአንድ ድምጽ አብላጫ ያለፈ ሳይሆን ብዙሃኑ የሚቀበሉትን ሃሳብ ያዘለ የውሳኔ ሃሳብ ማሳለፍ ይጠበቅበታል።
- ለመድረክ በዚያው ወቅት የሚደርስ ማስተካከያ ተጽፎ እንዲደርስና በአካልም ደብደቤውን ማድረስና ተጨማሪ ማብራርያ መስጠት ጨዋነት ብቻ ሳይሆን ስነምግባር ያለው አካሄድ ነው።
- ከእንግዲህ አንድነትን ወክለው በሲቀመንበሩ መሪነት ከመድረክ ጋር የሚደራደሩ ሁለት አባለት በም/ቤቱ መምረጥ ይጠቅማል።

# የመነጋገርያ ነጥቦች

1. በዛሬው አጀንዳ ዙሪያ ስላሉት ጭብጥ ሃቆች፡-

- የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በም/ቤቱ የተሰጠውን የኃላፊነትና የስልጣን ገደብ ተላልፏል።
- ከመድረክ ጋር በአደባባይ መቀላቀል ብቻ ሳይሆን የፓርቲውን ስም በጥገኝነት ለመድረክ ሰጥቶ ከመድረክ አመራር አካላት ጋር አንድ ላይ በመሆን መግለጫ ሰጥቷል፣ በመግለጫ ጽሑፉም ላይ የፓርቲውን ማኅተም አስፍሯል።
- በዚህም ድርጊቱ የአንድነትን/ቅንጅትን የጎላ ታሪክና ድርጅታዊ አቅም እንዲሁ ፓርቲውን ሕጋዊ ሰውነቱ በማይታወቅበት፣ የፖለቲካ አላማው እንዲሁም የአባላቱ ግለሰቦች የፖለቲካ ምኞት በግልጽ ከማይታወቅ ቡድን ጋር አንድነትን ገደቡ ባልተወሰነ ቅልቅል አስሮታል።
- የም/ቤቱ ስብሰባ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ በመድረክ፣ የኛ ስራ አስፈጻሚ አባላት በነበሩበት፣ የተወሰነው ዝርዝር መረጃ ደርሶትና የዚህ ድርጊት በአንድነት ላይ ስለሚኖረው ሁለገብ አደጋ በመስጋት ለወቅቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ውሳኔውን ለማስቀየር የሚያስችል ከረር ያለ ደብዳቤ ጽፎ ድርጊት በተግባር ሳይፈጸም 24 ሰዓት በፊት አቅርቦ ነበር።

2. ይህንን ግድፈት ለማረም የሚያስችል እርምጃች፡-

- በም/ቤቱ የአደባባይ መግለጫ ድርጊቱን መረዳም፣
- ለመድረክ በዚያው ወቅት የሚደርስ ማስተባበያ ጥቆማ እንዲደርስና በአካልም ደብዳቤውን ማድረስና ተጨማሪ ማብራርያ መስጠት፣
- ሁለትም ይሁኑ ሶስት አንድነትን ወክለው ከመድረክ ጋር ይነጋገሩ የነበሩት የአንድነት አባላት ከዚህ የውክልና ተግባር ታግደው ም/ቤቱ ሌሎች ሶስት ወይም ሁለት ወኪሎች መምረጥ፣
- ለጥፋተኞቹ፣ በወል የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባላት ላይም ሆነ ለወከሉት ግለሰብ አባሎች፣ ተጨማሪ እርምጃ ያስፈልጋል ብሎ ካታመነበት ከም/ቤቱ (ምናልባትም ከኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት) በተመረጠ ልዩ ኮሚቴ እንዲጠናና እንዲታይ ማድረግ።